ጥቅምት 27 2013
3·1·1/79/13

**በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ**

**በያሉበት፣**

**ጉዳዩ፡-የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የአፈጻጸም መመሪያ ስለመላክ፣**

የገንዘብ ሚኒስቴር ጥቅምት 05 ቀን 2013 ዓ.ም በቁጥር ገ/ኢ/1/2/41 በተጻፈ ደብዳቤ የተዘጋጀውን የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 67/2013 መላኩን በመግለጽ መመሪያው ስራ ላይ እንዲውል ከሚኒስቴር መ/ቤታችን ጽ/ቤት በቁጥር 1.0/36/13 በ25/02/2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ተልኮልናል፡፡

ስለሆነም በገንዘብ ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 67/2013 ለአፈጻጸም መላካችንን እየገለጽን፣ መመሪያው ተፈጻሚ ከሚደረግበት ጊዜ ጀምሮ የሚመለከታቸው ኃላፊዎችና የስራ ክፍሎች አውቀውት ተግባራዊ እንዲደረግ እያሳሰብን፣ የመመሪያውን 30(ሰላሳ) ገጽ ቅጂ በሀርድ ኮፒ እንዲሁም ሶፍት ኮፒ በታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ሥራ አስኪያጆች የኢ-ሜይ አድራሻ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬትም መመሪያው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ ወይም አገልግሎት ለሚሰጡ ወይም ከውጭ ወደ ሃገር ለሚያስገቡ ታክስ ከፋዮች ተደራሽ እንዲሆን እና መመሪያውን ተፈጻሚ እንዲያደርጉ በተቋሙ ድህረ-ገጽ እንድሁም የፌስ ቡክ አድራሻ ላይ እንዲጫን የዚህ ደብዳቤ ግልባጭ ተመዝግቦለታል፡፡

ከሰላምታ ጋር

**ማስረሻ ሽመልስ መንግስቴ**
**የኤክሳይዝ ታክስ አስተግባሪ**
**ግብረ-ሃይል አስተባባሪ**

**ግልባጭ//**

- ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ማጣጣምና ለክልሎች ደጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስና የጉምሩክ መረጃ ማብራሪያና የምክር አገ/ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**የገቢዎች ሚኒስቴር፣**

**አባሪዎች**

- ለከፍተኛ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመካከለኛ ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አ/አ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለምሥራቅ አ/አ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሰሜን ምዕራብ አ/አ/አነ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት
- ለሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት

**የገቢዎች ሚኒስቴር**

ታክስ-290
26/2/13



ቀን ጥቅምት 2 5 2013
Date
ቁጥር 10/36/13
Ref.No

ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ

ለህግ ተገዥነት ዘርፍ

ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ

ገቢዎች ሚኒስቴር

ጉዳዩ፡- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የአፈፃፀም መመሪያ ስለመላክ፣

ከገንዘብ ሚኒስቴር ጥቅምት 5 ቀን 2013 ዓ/ም በቁጥር ገ/ኢ/1/2/41 በተፃፈ ደብዳቤ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ለማስፈፀም የተዘጋጀውን መመሪያ በስራ ላይ እንዲውል ልኮልናል፡፡

በመሆኑም ለአፈፃፀም እንዲረዳ የመመሪያው 28 ገፅ ቅጂ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ የተላከ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

"ከሰላምታ ጋር"

ነቢዩ ሳሙኤል
የሚኒስትር ታክስ አማካሪና
የጽ/ቤት ተወካይ

እንዲያውቁት፣

- ለክቡር ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለሴቶችና ህፃናት ወጣቶች ዳይሬክቶሬት
- ለተቋማዊ ስጋት ስራ አመራር ሥነ-ምግባር ዳ/ት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክተሮች
- ለስትራቴጂ ፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
- ለስትራቴጂክ አጋርነት ዳይሬክቶሬት

ገቢዎች ሚኒስቴር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር / Ref.No 7/ኪ/1/2/41
ቀን / Date 05/02/2013

ለገቢዎች ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀጽ 42(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አዋጁን በተሟላ መልኩ ማስፈፀም የሚያስችል መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

ስለዚህ የተዘጋጀውን መመሪያ ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እየገለፅን የመመሪያው አንቀጽ 41 መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ በሚደነግገው መሠረት መመሪያው በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
ለክቡር የፊሲካል ፖሊሲና ፐብሊክ ፋይናንስ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

Letter Hab/GT

ስልክ Tel 251- 11- 155 24 00,22 66 98 / 251- 11- 155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96 / 251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

## የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 67/2013

ገንዘብ ሚኒስቴር

2013 ዓ.ም

# የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የአፈፃፀም
## መመሪያ ቁጥር 67/2013

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2011 አንቀጽ 42(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከዚህ የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ስለኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 67/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡ በአዋጁ ትርጉም ያልተሰጣቸው በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች የሚከተለውን ትርጉም ይይዛሉ፡-

ሀ/ "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አቅራቢ" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት፣ ለሽያጭ ለማዋል የሚገዛ ወይም የሚሸጥ ማናቸውም ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

ለ/ "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ጊዜ" ማለት በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ለታክሱ ባለሥልጣን የሚከፈልበት ጊዜ ነው፡፡

ሐ/ "የተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ" ማለት የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርትበት እና የሚያከማችበት ፈቃድ የተሰጠው ቅጥር ግቢ ነው፡፡

መ/ "የተፈቀደለት አምራች" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት ሰው ነው፡፡

ሠ/ "ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር" ማለት የተፈቀደለት አምራች ለታክሱ ባለሥልጣን የሚያቀርበው በሚቀጥለው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሚያመርታቸው ዕቃዎች ዋጋ ዝርዝር ሲሆን፣ በፋብሪካው ተመርተው ለዚሁ ፋብሪካ በግብዓትነት የዋሉ ጥሬዕቃዎችን ዋጋ ይጨምራል፡፡



Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No 1

ረ/ "ወደአገር የሚገባበት ቦታ" በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደኢትዮጵያ የሚገቡበት ወደብ፣ አውሮፕላን ማረፊያ ወይም ድንበር ነው፡፡

ሰ/ "አዋጅ" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ነው፡፡

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1/ ይህ መመሪያ:-

ሀ) ፈቃድ የተሰጣቸው ቢሆንም ባይሆንም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በሚያመርቱ ወይም ወደአገር በሚያስገቡ፣

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች በእጃቸው በሚገኝ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለባቸውን ወይም በማሳነስ የተከፈለባቸውን ዕቃዎች በሚያቀርቡ፣

ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2/ ይህ መመሪያ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ ከተዘጋጀው የአሠራር ማንዋል ጋር በአንድነት መነበብ አለበት፡፡

## ክፍል ሁለት

## <u>የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለሚያመርቱ ስለሚሰጥ ፈቃድ</u>

5. <u>የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት</u>

1/ ማናቸውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ 16 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡፡

ሀ) ማመልከቻው በተፈቀደው ቅጽ መሠረት መቅረብ አለበት፣

ለ) ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉት ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

(i) የንግድ ፈቃድና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን ጨምሮ የታክስ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ እንዲቀርቡ የሚጠይቃቸው ሰነዶች፣

(ii) አመልካቹ የሚጠቀምባቸውን የአመራረት ሂደቶች፣ እንደአግባብነቱ የማምረቻውን መሣሪያዎች፣ የአልኮል ማጣሪያዎች፣ የቢራ መጥመቂያ፣ የፈሳሽ ማከማቻ ኮንቴይነሮች፣ መሣሪያዎች፣ መገጣጠሚያዎች፣

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No 1

(iii) የአሠራር ሂደቱን የሚገልፅ የፅሑፍ ማብራሪያ፣

iv) ፈቃድ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበትን የማምረቻ ሕንፃ ፕላን፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች እንዲሁም ሕንፃው፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች የሚገኙበትን ሁኔታ እና አካባቢውን፣

(v) የእያንዳንዱን በፋብሪካው የተገጠመ የማምረቻ መሣሪያ የማምረት አቅም በዝርዝር፣

(vi) የማምረቻ መሣሪያዎችን ማስረጃዎች እና መግለጫዎች፣

(vii) በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ የዚህ ዓይነቱን ፈቃድ ለማግኘት እንዲሟሉ የሚጠበቁ መሣሪያዎችን፣ የአመራረት ሥርዓት ወይም ሌላ ተፈላጊ ሁኔታ፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ በተፈቀደው ቅጽ መሠረት መሆን አለበት፡፡

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ካልተመዘገበ በስተቀር የሚከተሉትን ሥራዎች ማከናወን አይችልም፡-

ሀ) የሲጋራ ማምረቻ ወረቀት እና የሲጋራ ማሸጊያ ዕቃዎችን ወደአገር ማስገባት፣

ለ) ጥሬ ወይም በምርት ሂደት ያላለፈ ትምባሆን ወደአገር ማስገባት፣

ሐ) ኤታኖል ወደአገር ማስገባት፣

መ) በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ለ) የተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ግብዓቶች ወደአገር ማስገባት፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና (ለ) ለተመለከቱት ዕቃዎች በአስመጪነት ሊመዘገብ የሚችለው የትምባሆ ምርቶችን ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ብቻ ነው፡፡

4/ በኤታኖል አስመጪነት ሊመዘገቡ የሚችሉት፣

ሀ) የአልኮል መጠጦችን ለማምረት ፈቃድ የተሰጣቸው፣

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የማይከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የሚውሉ የማጣሪያ መሣሪያዎችን ወደአገር ለማስገባት የሚችሉት የተመዘገቡ ሰዎች ብቻ ናቸው፣

Ministry of Revenues Records & Documentation No 1

5/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለመመዝገብ ማመልከቻ የሚቀርበው፣

ሀ) በተፈቀደው ቅጽ መሠረት፣

ለ) የታክሱ ባለሥልጣን ከሚጠይቃቸው ሰነዶች ጋር በአንድነት መሆን አለበት፣

6. <u>የማምረቻ ቦታዎችን ስለመገምገም</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እና 9 መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብ የታክሱ ባለሥልጣን የማምረቻ ቦታውን እና የአመራረቱን ሂደት ማመልከቻው ተሟልቶ በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በቦታው በመገኘት መገምገም አለበት፡፡

7. <u>የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ስለማግኘት</u>

1/ ማናቸውም ሰው ከገቢዎች ሚኒስቴር የተሰጠ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ሳይኖረው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 የተዘረዘሩ ሥራዎችን ሊያከናውን አይችልም፡፡

2/ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት በተፈቀደለት አምራች እና በታክሱ ባለሥልጣን መካከል እንደተፈፀመ ውል ይቆጠራል፡፡

3/ በፈቃዱ የተመለከቱ የውል ቃሎችንና ሁኔታዎችን የሚጥስ የተፈቀደለት አምራች በአዋጁ አንቀጽ 39 መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

4/ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የሚከተሉትን መረጃዎች የሚይዝ ሊሆን ይገባል፡-

ሀ) የተፈቀደለትን አምራች ስም፣

ለ) የተፈቀደለትን አምራች የግንኙነት አድራሻ (ኢሜይል፣ ፋክስ፣ ስልክ)፣

ሐ) ፈቃዱ ተፈፃሚ መሆን የሚጀምርበትን ቀን፣

መ) የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያመርትበትን ፋብሪካ እና የዋናው መሥሪያ ቤት አድራሻ፣

ሠ) የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ እንዲጠቀምባቸው በታክሱ ባለሥልጣን የተፈቀደለትን መሣሪያዎች ዝርዝር፣

ረ) የሚያመርተውን ምርት ዓይነት

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No 1

5/ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የተፈቀደለትን አምራች የሥራ አፈፃፀም መሠረት በማድረግ የንግድ ሥራውን የሚያካሂድባቸውን ሁኔታዎች የሚይዝ ሊሆን ይችላል፡፡

6/ የተፈቀደለት አምራች በፈቃዱ በተዘረዘሩ መሣሪያዎች ለመጠቀም የሚችለው በፋብሪካው በተመለከተው አድራሻ ብቻ ነው፡፡

7/ የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች የሚመረቱበትን አድራሻ ወይም መሣሪያ ከመለወጡ በፊት፣ ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን በማስታወቅ በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ መጠየቅ አለበት፡፡

8/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች የሚመረቱበትን አድራሻ ወይም የመሣሪያዎች መለወጥ ለታክሱ ባለሥልጣን ሳያስታውቅ እና በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ ሳይደረግ አድራሻውን ወይም መሣሪያዎችን የለወጠ ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ 39 መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

9/ የተፈቀደለት አምራች ፋብሪካ እና የማምረቻ መሣሪያዎች በአዋጁ የተደነገገውን የሚያሟሉ መሆኑ በታክሱ ባለሥልጣን ባለሙያዎች ጉብኝት ሳይረጋገጥ የኤክሳይዝ ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም፡፡

8. <u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1/ አመልካቹ ያቀረበው ማመልከቻ ከተመረመረ እና የማምረቻ ቦታው በታክሱ ባለሥልጣን ባለሙያዎች ከተገመገመ በኋላ መስፈርቶቹ መሟላታቸው ሲረጋገጥ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ይሰጣል፣

2/ የተፈቀደለት አምራች በአመራረቱ ሂደት ወይም ሌላ ማናቸውም ፈቃዱ በተሰጠበት ሁኔታ ላይ ለውጥ ማድረግ በሚፈልግበት ጊዜ አስቀድሞ ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ እንዲችል በፈቃዱ ላይ የሚመለከተው የታክሱ ባለሥልጣን አድራሻ መመልከት አለበት፡፡

9. <u>አዲስ አምራቾች</u>

1/ በአዋጁ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ያልተሰጠው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የሚፈልግ ሰው የማምረት ሥራውን ለመጀመር ካቀደበት ቀን 30 ቀን በፊት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ እንዲሰጠው ለታክሱ ባለሥልጣን ማመልከት አለበት፡፡



Ministry of Revenues Records & Documentation No 1

2/ የማመልከቻው ቅድ አዲስ የሚጀመረውን የንግድ ሥራ በሚመለከት የተሟላ መረጃ ማግኘት የሚያስችል መሆን አለበት፤ በተለይም የንግድ ሥራው የሚመሩ ኃላፊዎች፣ የሚመረተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ዓይነት፣ የማምረቱ ተግባር የሚከናወንበትን ቦታ፣ የግብዓቱን ዓይነት፣ የግብዓት ምርት ጥመርታውን እና የማምረቻ መሣሪያውን ዓይነት የሚያካትት መሆን አለበት፡፡

3/ የማምረቻ ቦታው በታክሱ ባለሥልጣን ከመጐብኘቱ እና አመልካቹ የማመልከቻውን ቅጽ በሚገባ ሞልቶ ከማቅረቡ በፊት ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም፡፡

10. ተጨማሪ ፋብሪካ ስለማቋቋም

1/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በተሰጠው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ላይ ያልተመለከተ አዲስ ፋብሪካ ለማቋቋም ያቀደ እንደሆነ በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ወይም አዲስ ፈቃድ እንዲሰጠው መጠየቅ አለበት፡፡

2/ ማናቸውም ሰው የታክሱ ባለሥልጣን ባለሙያዎች የማምረቻ ቦታውን ጐብኝተው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት መጀመር አይችልም፡፡

3/ ፈቃድ ባልተሰጠው ፋብሪካ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያመርት ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክሱን መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰው በአዋጁ መሠረት አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣት ይቀጣል፡፡

11. የኤክሳይዝ ፈቃድን ወይም ምዝገባን ስለማገድ እና ስለመሠረዝ

1/ በአዋጁ አንቀጽ 20 ከተመለከተው በተጨማሪ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የታክሱ ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ የሚወክለው የኤክሳይዝ ፈቃድን ማገድ ይችላል፡፡

ሀ) ከአምራቹ አቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው በተፈቀደለት አምራች የተመረተ የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለበት ዕቃ ይዞ የተገኘ እንደሆነ፣

ለ) የተፈቀደለት አምራች በፈቃዱ ወይም በምዝገባው ከተመለከተው ውጪ በሆነ ተግባራት ተሠማርቶ የተገኘ እንደሆነ፣

ሐ) ፈቃድ የተሰጠበት ተግባር በአዋጁ ወይም በሌላ ሕግ የተከለከለ እንደሆነ፣

መ) የተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ ወይም መሣሪያ ከታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድ ውጪ ተለውጦ የተገኘ እንደሆነ፣


Ethiopian Ministry of Revenues

2/ በአዋጁ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ምዝገባ የታገደ እንደሆነ ባለፈቃዱ፣

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረቱን ተግባር ወዲያውኑ ማቆም፣ እና

ለ) የታክሱ ባለሥልጣን በሚያቀርባቸው ሁኔታዎች መሠረት መፈፀም አለበት፡፡

3/ በአዋጁ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ወይም ምዝገባ የተሠረዘ እንደሆነ፦

ሀ) ባለፈቃዱ፡-

(i) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረት ወይም ወደአገር የማስገባት ተግባሩን ማቆም፣

(ii) በእጁ በሚገኙ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል፣

(iii) የታክሱ ባለሥልጣን በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች፣ ጥሬዕቃዎች፣ መሣሪያዎች፣ ቁሳቁሶች መሸጥ፣ አለበት፡፡

ለ) የታክሱ ባለሥልጣን፣

(i) የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወደሌላ ቦታ እንዲያዘዋውር፣

(ii) የመንግሥትን ገቢ ለመሰብሰብ እና አዋጁን ለማስፈፀም እንዲቻል የተፈቀደለትን አምራች ፋብሪካ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ፣ ይችላል፡፡

4/ ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "ፋብሪካን በቁጥጥር ስር ማድረግ" ማለት በፋብሪካው ውስጥ የተፈቀደለት አምራች የሚያከናውነው ማናቸውም ተግባር በታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድና እውቅና እንዲከናወን ማድረግ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር

### 12. በማምረቻ ቦታዎች ወይም በማስተላለፊያ መስመሮች ላይ ምልክት ስለማድረግ

1/ የተፈቀደለት አምራች፡-

ሀ) የታክሱ ባለሥልጣን በሚጠይቀው መሠረት በማምረቻ ቦታው ዋና የመግቢያ በር እና በሌላም አስፈላጊ ቦታ ላይ በአማርኛና በአካባቢው የሥራ ቋንቋ፡-

(i) "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማምረቻ" እና

(ii) የተፈቀደለትን አምራች ስም እና የፈቃድ ቁጥር የያዘ ፅሑፍ መለጠፍ አለበት፡፡

ለ) በምርቱ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስተላለፊያ መስመሮች በቋሚነት የተገጠሙ እና መላውን ርቀት በትክክል ለመመርመር የሚያስችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ሐ) የማከማቻ እና የማስተላለፊያ መስመሮች ኢንዱስትሪው የሚጠየቀውን ደረጃ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው፡፡

መ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በሚመረቱባቸው፣ ለሽያጭ በሚዘጋጁባቸው ወይም በሚከማቹባቸው መሣሪያዎች ላይ በዘይት ቀለም ምልክት ማድረግ አለበት፡፡

ሠ) የተፈቀለት አምራች የታክሱን ባለሥልጣን በሚያረካ ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሣሪያ ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች አኳኋን ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ የተገጠመባቸው እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡

ረ) ለኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ ሲባል መቆለፍ ወይም ማሸግ እንዲቻል የታክሱ ባለሥልጣን በሚጠይቀው መሠረት መሣሪያዎችን ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ በሚያስችል መንገድ ማዘጋጀት አለበት፡፡

ሰ) የታክሱን ባለሥልጣን በሚያረካ ሁኔታ፡-

(i) በእያንዳንዱ የማምረት ሂደት የምርት ርክክብ የሚፈፀምባቸው የማስተላለፊያ መስመሮች በተለያየ የዘይት ቀለም እንዲቀቡ እና ቀለሙ እንዳይጠፉ በየጊዜው እንዲታደስ ማድረግ አለበት፡፡

(ii) ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሣሪያ ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ መግጠም፣ አለበት፡፡

ሸ) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሰ) አፈፃፀም የማጣሪያ ፋብሪካ ባለቤት በተሟላ አኳኋን እና ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መንገድ የማስተላለፊያ መስመሮችን የሚከተለውን የዘይት ቀለም ዓይነት መቀባት አለበት፡-

(i) የአልኮል መጠጥ - ቀይ

(ii) ቢራ - ሰማያዊ

(iii) ሞላሰስ - አረንጓዴ

(iv) የሚጠራ ወይን - ቡናማ

(v) ውሃ - ቢጫ

(vi) ናፍጣ - ጥቁር

ቀ) ለታክሱ ባለሥልጣን አስቀድሞ በማስታወቅ ከታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር የአመራረቱን ሂደት ወይም አካሄዱን መለወጥ፣ ማከማቻ ወይም መሣሪያ መጨመር፣ የለበትም።

2/ ሀ) በተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ የጽሕፈት ሥራ የሚከናወንበት ቢሮ፣ የማምረቻው ቦታ፣ የጥሬዕቃ መጋዘን፣ የምርት መጋዘን የተለያየ መሆን አለባቸው።

ለ) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) አፈፃፀም ለእያንዳንዱ ተግባር የተመደበው ቦታ ጥበቃ የሚደረግለት እና አንዱ ከሌላው ጋር የማይገናኝ እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስን በሚገባ መሰብሰብ እንዲቻል ለይቶ ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ የሚያስችል አካል የተገጠመለት መሆን አለበት።

3/ ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የተፈቀደለት አምራች እና የተመዘገበ አስመጪ ወደ አገር የሚያስገባቸውን ዕቃዎች የሚያከማችበት በታክሱ ባለሥልጣን የተፈቀደ የተለየ መጋዘን ሊኖረው ይገባል።

## 13. <u>ፋብሪካውን በሩቅ መቆጣጠር የሚያስችል መሣሪያ ስለመግጠም</u>

1/ የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ የሚከናወነውን እንቅስቃሴ በሩቅ ማየት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሥርዓት መግጠም አለበት።

2/ የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ መመሪያ መሠረት ሊገጠም የሚገባውን የቴክኖሎጂ መሣሪያ ዝርዝር ባህሪያት ይወስናል።

3/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀም የታክሱ ባለሥልጣን ፋብሪካውን በሩቅ ማየት የሚያስችለውን የቴክኖሎጂ ሥርዓት የመጠቀም ያልተገደበ መብት ይኖረዋል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው የቴክኖሎጂ ሥርዓት የታክስ ባለሥልጣኑ በሚጠይቀው መሠረት ደህንነቱ የተጠበቀ የምስል ማከማቻ እና ምስልን እና ሌላን መረጃ በዲጂታል ሥርዓት በቀጥታ ማስተላለፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

## 14. <u>የአመራረት ሂደትን በቴክኖሎጂ ስለማስደገፍ</u>

1/ የታክሱ ባለሥልጣን የተወሰኑ የተፈቀደላቸው የማምረቻ ቦታዎች በእያንዳንዱ ደረጃ ያሏቸው የአመራረት ሂደት በአውቶማቲክ የአመራረት ሂደት የታገዘ እንዲሆን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2/ የአልኮል መጠጥ ማምረቻ ፋብሪካዎችን በሚመለከት ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ግዴታ ሊጣልባቸው የሚችለው የፋብሪካው የማምረት አቅም በሰዓት ከ500 (አምስት መቶ) ጠርሙስ በላይ ሲሆን ነው፡፡

## 15. <u>የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች</u>

1/ የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሠረት በማምረቻ ቦታዎች ሊታከሉ የሚገባ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ እንዲሁም ሌሎች መሣሪያዎችን ተፈላጊ ባህሪያት በጋዜጣ እና በድረገፁ ላይ ማሠራጨት አለበት፡፡

2/ በታክሱ ባለሥልጣን የሚፈቀዱት በማምረት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች የጥሬ ዕቃዎችን፣ የግብዓቶችን እና የአላቂ ዕቃዎችን መጠን በትክክል ማወቅ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡

3/ የጥሬዕቃ እና የአላቂ ምርቶች ማከማቻ ጋኖች በጋኑ ውስጥ ያለውን መጠን በትክክል ማወቅ የሚያስችል የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

4/ በዚህ መመሪያ መሠረት ጥቅም ላይ የሚውሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች የታክሱ ባለሥልጣን በሚወሰነው መሠረት በምርቱ ሂደት በእያንዳንዱ የምርት ሠንሰለት ላይ መገጠም አለባቸው፡፡

5/ የተፈቀደለት አምራች፡-

ሀ) የታክሱ ባለሥልጣን ለሚያካሂደው ቁጥጥር እና ስሌት በሚያመች መንገድ መቁጠሪያ እና መለኪያ ያላቸውን ጋኖች ወይም ማከማቻዎች የማዘጋጀት፣ በትክክል የሚሠሩ መሆኑን በየጊዜው የማረጋገጥ፣ እና

ለ) በመለኪያ እና በመቁጠሪያ መሣሪያዎች ላይ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ የተደረገውን ዕድሳት የሚያሳይ መዝገብ የማዘጋጀት፣ መሣሪያዎቹ በትክክል የሚሠሩ መሆኑን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

16. <u>በምርቶች፣ በመያዣዎች እና በማሸጊያዎች ላይ ምልክት (ሌብል) ስለማድረግ</u>

1/ ከታክስ ነፃ የሆኑ፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማሸጊያዎች ለመከታተል እና ለይቶ ለማወቅ በሚያስችል አኳኋን የተለየ ምልክት ሊደረግባቸው ይገባል።

2/ ለጅምላ ሽያጭ የሚውሉ ዕቃዎችን የሚይዝ እያንዳንዱ ማሸጊያ ወይም መያዣ ወይም መጠቅለያ በሚከተለው አኳኋን ህትመት ሊደረግበት ይገባል፦

ሀ) ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ከሆነ፣ የመጨረሻ መድረሻውን አገር የሚያሳይ ፅሑፍ፣

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ፣ "ለአገር ውስጥ ፍጆታ" የሚውል የሚል ፅሑፍ፣

ሐ) ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች ለሚሸጡበት መደብር ወይም ለዲፕሎማቲክ ሱቆች የሚሸጥ ከሆነ "ከታክስ ነፃ" የሚል ፅሑፍ፣

3/ ስዚህ አንቀጽ አፈፃፀም የታክሱ ባለሥልጣን ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ዕቃዎችን ለመለየት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ሊደረግ የሚገባውን ምልክት በመመሪያ ሊወሰን ይችላል።

17. <u>በጥሬዕቃ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር</u>

1/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የሚውሉ ጥሬዕቃዎች መጠናቸውን በትክክል ለማወቅ ለሚደረገው ቁጥጥር በሚያመች አኳኋን ደህንነቱ በተጠበቀ ክፍል ወይም መጋዘን መቀመጥ አለባቸው።

2/ በተፈቀደለት ማምረቻ ውስጥ ለምርት ተግባር እንዲውሉ ለማድረግ ወይም አደጋ በማጋጠሙ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ሳይፈቀድ ጥሬ ዕቃዎችን ማውጣት አይችልም።

3/ የአልኮል ማጣሪያ ባለቤት ከኤቲል አልኮል በስተቀር ማናቸውንም ሌላ አልኮል በታክሱ ባለሥልጣን በሚወሰነው መሠረት ለሰው ጥቅም እንዳይውል ከመደረጉ በፊት በመጋዘን ማስቀመጥ አይችልም።

18. <u>የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከተመረቱ በኋላ በመጋዘን ስለማስቀመጥ ወይም ስለማስረከብ</u>

1/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረት ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ "የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ" በመባል ወደሚታወቅ ክፍል መዘዋወር እና በዚህ መመሪያ መሠረት ከተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ውጪ እስከሚደረጉ ድረስ በዚሁ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡ ሆኖም የተጣራ አልኮል መቀበያ ጋኖች የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ እንደሆኑ ይቆጠራል፡፡

2/ የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል በር ላይ "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል" የሚል ፅሑፍ መለጠፍ አለበት፡፡

3/ የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን የተመረቱ ዕቃዎች ከማከማቻነት ውጪ ለሌላ ለማናቸውም ተግባር እንዲውል ማድረግ አይቻልም፡፡

4/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ለቆጠራ በሚያመች አኳኋን በኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለባቸው፡፡

5/ ማናቸውም ሰው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልበት ዕቃ መያዣ ጠርሙስ ወይም ማሸጊያ አምራቹን ለይቶ ማወቅ የሚያስችለው ልዩ ምልክቱ (ሌብል)፣ የአምራቹ ስም፣ የተመረተበት ቦታ እና ቀን፣ አድራሻው፣ የተከታታይ ምርት ቁጥር፣ የባር ኮድ ወይም ሌላ ተጨማሪ ምልክት ሳይደረግበት በፊት ከኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል ማውጣት ወይም እንዲወጣ ማድረግ ወይም መፍቀድ የለበትም፡፡

6/ ለውጭ ገበያ ወይም ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው ሊሸጡ የተመረቱ ዕቃዎች ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች መንገድ ከሌሎች ዕቃዎች ተለይተው መቀመጥ አለባቸው፡፡

7/ የተፈቀደለት አምራች ከተሸጡ በኋላ ወደተመረቱበት ፋብሪካ የተመለሱ ዕቃዎች የሚቀመጡበት የተለየ መጋዘን ሊኖረው ይገባል፡፡

19. <u>ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና ከታክስ ነፃ ሆነው የሚሸጡ ዕቃዎች</u>

1/ የተፈቀደለት አምራች የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካጋጠሙ በዕቃዎቹ ላይ ታክሱን እንዲከፍል ይገደዳል፡-

ሀ) ለውጭ ገበያ የተመረቱ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የተሸጡ እንደሆነ፣

ለ) ከታክስ ነፃ ሆነው ስለሚሸጡበት ወይም ታክሱ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ በአዋጁ የተመለከተው ያልተሟላ እንደሆነ፣

2/ የተፈቀደለት አምራች ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና የተከፈለባቸው ታክስ ተመላሽ የሚደረግ ዕቃዎችን የማስታወቅ እና የማንንዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

3/ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ የአልኮል መጠጦችን የሚሸጥ የቀረጥ ነፃ መደብር እነዚህን ዕቃዎች ወደአገር ለማስገባት የሚችለው "ከቀረጥ ነፃ" የሚል ምልክት የተደረገባቸው ሲሆን ብቻ ነው፡፡

## 20. <u>የሂሳብ መዝገብን ስለመያዝ</u>

1/ የተፈቀደለት አምራች በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2016 ድንጋጌዎች መሠረት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መያዝ ያለበት የሂሳብ መዝገብ፣

ሀ) በሚነበብ እና ሊጠፋ በማይችል አኳኋን በጽሕፈት መሣሪያ የተዘጋጀ፣ የታተመ ወይም የተባዘ ሊሆን የሚገባው ሲሆን፣ ከመፅደቁ በፊት የተደረገ እርማት ወይም ለውጥ ሲኖር የተደረገውን ለውጥ ወይም እርማት በትክክል ለማወቅ የሚያስችል፣ እርማቱን ያከናወነው ሰው ፊርማ እና የታረመበት ቀን የተባፈበት፣

ለ) በተፈቀደ አኳኋን በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ መንገድ የተዘጋጀ እና በተፈቀደው አኳኋን ካልሆነ በስተቀር ለውጥ ያልተደረገበት፣

መሆን አለበት፡፡

3/ የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ ከተመለከተው ውጪ የተዘጋጀን የሂሳብ ሰነድ ወይም ማስረጃ ላለመቀበል ወይም በዚህ ሰነድ መሠረት ሥራዎችን ላለማከናወን ይችላል፡፡

4/ የታክሱ ባለሥልጣን ማናቸውም የሂሳብ ሪፖርት ሊቀርብ የሚገባበትን ቅጽ ወይም ለአዋጁ እና ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተቀባይነት የሚኖራቸውን ሰነዶች ዓይነት ሊወስን ይችላል፡፡

## 21. <u>ልዩ ምልክትን (ሌብል) ስለማሳወቅ</u>

1/ ማናቸውም የተፈቀደለት ሰው በተፈቀደው ቅጽ መሠረት እና የታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው እና በሚያፀድቀው ዝርዝር መሠረት ልዩ ምልክቱን ሳያስታውቅ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ለሽያጭ በጠርሙስ ወይም በሌላ መያዣ ማሸግ አይችልም፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የታክሱ ባለሥልጣን ማመልከቻ ሲቀርብለት ሁኔታዎችን በመወሰን የተፈቀደለት አምራች ለሙከራ የሚውሉ ምርቶችን እንዲያመርት ሊፈቅድ ይችላል።

22. <u>የምርት መከታተያ ሥርዓት</u>

1/ የታክሱ ባለሥልጣን የተፈቀደለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራች ወይም አስመጪ የምርት ሂደቱን መከታተል የሚያስችል የሂሳብ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሊያዝ ይችላል።

2/ የምርት መከታተያው ሥርዓት፦

ሀ) የምርትን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ወይም ማሳየት የሚያስችል መሣሪያ፣

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን በተፈቀደለት አምራች የተመረቱ ወይም ወደአገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን ብዛት ለመቆጣጠር፣ ለመመዝገብ እና መረጃውን ለማስተላለፍ የሚያስችል መሣሪያ፣ መሆን አለበት።

3/ የምርት መከታተያው ሥርዓት፦

ሀ) በማምረቻው ቦታ በምርት ሠንሰለት ውስጥ በእያንዳንዱ የማሸጊያ ወይም የማተሚያ መሣሪያ ላይ ሊገጠም፣ እና

ለ) ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎችን ለመቆጣጠር በታክሱ ባለሥልጣን በሚወስነው አኳኋን ሊገጠም፣ ይገባል።

4/ አዲስ ወይም የተሻሻለ የምርት መከታተያ ሥርዓት መግጠም አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ የታክሱ ባለሥልጣን ለአምራቹ ወይም ለአስመጪው መሣሪያው ከሚገጠምበት ጊዜ በፊት የሚከተሉትን የያዘ ማስታወቂያ መስጠት አለበት፦

ሀ) አዲሱ መሣሪያ የምርት መከታተያውን ሥርዓት የተሻለ ለማድረግ አስፈላጊ መሆኑን፣

ለ) በእያንዳንዱ የምርት ሠንሰለት ውስጥ የሚደረገውን የማስተካከያ ሥራ ባህሪያት፣ እና

ሐ) በኮምፒውተሮች እና በሌሎች መሣሪያዎች ላይ መሣሪያው የሚገጠምበትን እና የሚሠራበትን ሁኔታ፣

5/ የተፈቀደለት አምራች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ወይም የማይሠሩ የምርት መስመሮች በሚከተለው አኳኋን ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፦





...of Revenues ...ocumentation No 1

ሀ) የማይሠሩ መስመሮችን በ24 ሰዓት ውስጥ፣ ወይም

ለ) አምራቹ ምርቱን ከ24 ሰዓት በላይ የሚያቋርጥ ከሆነ የምርት ሂደቱ በተቋረጠ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ፣

6/ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የታክሱ ባለሥልጣን የምርት መስመሮችን መቆጣጠር አለበት፡-

ሀ) የተፈቀደለት አምራች በዚህ አንቀጽ መሠረት የምርት መስመሮች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ወይም የማይሠሩ መሆኑን ካስታወቀ፣ ወይም

ለ) የምርት መስመሮች የማምረት አቅም ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ፣

7/ የታክስ ባለሥልጣን በዚህ መመሪያ መሠረት የምርት መስመሮችን የተቆጣጠረ በሚሆንበት ጊዜ የተፈቀደለት አምራች የታሸገው የምርት መስመር እንዲከፈትለት ለማድረግ አምራቹ ማምረት የሚጀምርበትን ቀንና ሰዓት ጭምር የያዘ የአመራረቱን የጊዜ ሠሌዳ የሚያሳይ ሪፖርት ለታክሱ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት ስለማከናወን - በዋጋው በመቶኛ

### 23. የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚቋቋምበት ጊዜ

1/ ሽያጭ የተከናወነ ቢሆንም ባይሆንም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች ከተመረቱበት የተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ በወጡበት ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል፡፡

2/ በታክስ ባለሥልጣኑ የተፈቀደው የብክነት መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ ማብራሪያ ወይም ማስረጃ ሊቀርብባቸው ያልቻለ በቆጠራ ጊዜ ያልተገኙ ወይም የጠፉ ዕቃዎች በአዋጁ ከተደነገገው ቅጣት በተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

### 24. የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት ስለሚሆን ዋጋ

1/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በዕቃው ዋጋ ላይ ተመስርቶ በሚሆንበት ጊዜ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

2/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ ሆኖ የሚቆጠረው፡-



Ethiopian Ministry of Revenues Documentation No 1

ሀ) ለታክሱ ባለሥልጣን በእያንዳንዱ ወር ከ30ኛው ቀን በፊት በሚቀጥለው ወር ከፋብሪካው የሚወጡ ዕቃዎች የሚቀርበው ዋጋ ዝርዝር ይሆናል፡፡

ለ) ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የዋጋ ዝርዝር ለእያንዳንዱ ምርት ዓይነት፣ መያዣ እና የመያዣ ዓይነት የሚኖረውን ዋጋ የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡

ሐ) ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆነው ምርቱን ወደገዥው ለማድረስ የሚወጣውን የትራንስፖርት ሂሳብ የሚጨምር አይሆንም፣

መ) በአዋጁ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክሱ ባለሥልጣን ምርቱ የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልበት ወደገበያ መቅረቡን ወይም ታክስ ከፋዩ የገለፀው ዋጋ ከገበያ ዋጋ በታች መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ዋጋውን ይወስናል፡፡

ሠ) በአዋጁ አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ትክክለኛ ዋጋን መሠረት በማድረግ የሚከፈለውን ታክስ የሚወስነው ታክስ ከፋዩ ያስታወቀው ዋጋ ከገበያ ዋጋ በታች ከሆነ፣ ምርቱ ታክስ ሳይከፈልበት ለገበያ ከቀረበ፣ ወይም ምርቱ ፈቃድ በሌለው ሰው የተመረተ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

ረ) ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ሆኖ የሚቆጠረውና ለኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ መሠረት የሚሆነው ሌላ የተፈቀደለት አምራች ለተመሳሳይ ዕቃዎች የሚያስከፍለው ዋጋ ሊሆን ይችላል፡፡

ሰ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ከመያዣው ጋር አብሮ የሚሸጥ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው በጠቅላላው ዋጋ ላይ ይሆናል፡፡ ሆኖም መያዣው ተመላሽ የሚደረግ ከሆነ በመያዣው ዋጋ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልም፡፡

ሸ) የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን የመጨረሻ ምርቶች ለማምረት የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸውን ጥሬዕቃዎች የሚጠቀም በሚሆንበት ጊዜ የሚያዘጋጀው የዕቃዎች ዋጋ ዝርዝር የእነዚህን ጥሬዕቃዎች ዋጋ የሚጨምር መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም የንፁህ አልኮል በሊትር የሚኖረው ዋጋ እና የትምባሆ ቅጠል በኪሎ ግራም የሚኖረው ዋጋ በዝርዝሩ ውስጥ መካተት ይኖርበታል፡፡

25. <u>ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር አቀራረብ</u>

1/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚከናወንበት ዋጋ ግልፅ እንዲሆን እና አምራቾች በእኩል መወዳደር እንዲችሉ እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች የምርቱን ዋጋ ዝርዝር በምርት ዓይነት፣ በመያዣው መጠን እና ዓይነት እንዲሁም ለገበያ በሚውልበት ቦታ በመለየት ለታክሱ ባለሥልጣን በየወሩ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር የሚዘጋጅበትና የሚቀርብበት ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ አምራቾች በተዘጋጀው ማንዋል ውስጥ በዝርዝር ይመለከታል፡፡

3/ የእያንዳንዱን የምርት ዓይነት፣ የነጠላውን መጠን እና ዓይነት የሚያሳየው የዋጋ ዝርዝር የእያንዳንዱን ምርት የማምረቻ ወጪ እና የትርፍ ህዳግ የያዘ ሊሆን ይገባል፡፡

4/ ዕቃው ለታክሱ ባለሥልጣን በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ከተመለከተው ዋጋ በላይ የተሸጠ እንደሆነ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆነው በደረሰኙ ላይ የተመለከተው ዕቃው የተሸጠበት ትክክለኛ ዋጋ ይሆናል፡፡

5/ ዕቃው ለታክሱ ባለሥልጣን በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ከተመለከተው ዋጋ በታች የተሸጠ እንደሆነ ወይም ከተፈቀደለት ፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ ዋጋው ያልተከፈለበት ከሆነ ከፋብሪካው በወጣው ዕቃ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው በቀረበው የዋጋ ዝርዝር በተመለከተው ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡

6/ ዕቃው ከፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ የሚዘጋጀው የዕቃ ማስረከቢያ ሰነድ እና/ወይም ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል፡-

ሀ) ዕቃው ከፋብሪካው የወጣበትን ቀን፣

ለ) የዕቃውን ማስረከቢያ ቦታ፣

ሐ) የደንበኛውን ስም ወይም ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካ የሚወጣ ከሆነ ይህንኑ፣

መ) ደንበኛው ከተፈቀደለት አምራች ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ከሆነ ይህንኑ፣

ሠ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዓይነት፣

ረ) የዕቃዎቹን ብዛት፣

ሰ) የእያንዳንዱን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ዋጋ፣

ሸ) ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ፣

26. <u>የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ</u>

1/ የእያንዳንዱ ወር የኤክሳይዝ ታክስ ታክሱን የመክፈል ግዴታ ከተቋቋመበት ወር ቀጥሎ ያለው ወር 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ለታክሱ ባለሥልጣን መቅረብ አለበት፡፡

2/ የተፈቀደለት አምራች ታክሱን የመክፈል ግዴታ ከተቋቋመበት ወር ቀጥሎ ባለው 30 ቀን ጊዜ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክሱን ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

3/ ከዋጋ ዝርዝር፣ ከማስረከቢያ ሰነድ እና ከደረሰኝ ጋር ማመሳከር እንዲቻል በኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ቅጽ ውስጥ የእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ዓይነት እና ለሽያጭ ከተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ወጥቶ ሳይሸጥ የተመለሰው ተለይቶ ማስታወቂያ ሊቀርብበት ይገባል፡፡

4/ የታክሱ ባለሥልጣን በእያንዳንዱ የታክስ ማስታወቂያ ላይ የተመለከተውን መረጃ በተፈቀደለት አምራች ከሚያዘው የምርት፣ በመጋዘን የሚገኝ ዕቃ እና የሽያጭ መረጃ ጋር ማመሳከር አለበት፡፡

5/ የተፈቀደለት አምራች የታክስ ማስታወቂያውን ትክክለኛነት የሚያስረዱ ደረሰኞችን፣ የዕቃ ማስረከቢያ ሰነዶችን እና የየዕለቱን የኤክሳይዝ ታክስ መረጃ በሚገባ መያዝ አለበት፡፡

6/ የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ መረጃዎችን በሚገባ ያልያዘ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 39 መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ከመሆኑ በተጨማሪ ካልተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ጋር እጥፍ የሆነ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃዱን የመሠረዝ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡፡

27. <u>የዕቃ ቆጠራ እና የጠፉ ዕቃዎች</u>

1/ እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ ጥሬዕቃዎችን ጨምሮ በፋብሪካው ውስጥ በሚገኙ ዕቃዎች ላይ በየዓመቱ የተሟላ ቆጠራ ማካሄድ አለበት፡፡

2/ ከዚህም በተጨማሪ የተፈቀደለት አምራች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያሳይ ተከታታይነት ያለው ወርሀዊ ቆጠራ ማካሄድ አለበት፡-

ሀ) በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ በፋብሪካው ውስጥ የሚገኘውን ጥሬዕቃና የመጨረሻ ምርት፣

ለ) አዲስ ወደፋብሪካው የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን፣

ሐ) በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬዕቃዎችን፣

መ) በፋብሪካው የተመረቱ የመጨረሻ ምርቶችን፣

ሠ) በፋብሪካው ተመርተው ወደፋብሪካው መጋዘን የገቡ ዕቃዎችን

ረ) የኤክሳይዝ ታክስ ተከፍሎባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ ዕቃዎችን፣

ሰ) የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ ዕቃዎችን፣

ሸ) የታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሠረት በአደጋ ምክንያት ከጥቅም ውጪ የሆኑ ዕቃዎችን፣

3/ የተፈቀደለት አምራች ለውጭ ገበያ የተላኩ ዕቃዎችን የሚመለከት የተሟላ መረጃ መያዝ አለበት።

4/ ዕቃዎች የጠፉ መሆኑን የሚያረጋግጥ የዕቃው መጥፋት በታወቀበት ጊዜ ወዲያውኑ ሪፖርት የተደረገና አግባብ ባለው የፀጥታ አካል ምርመራ ተካሂዶ የዕቃው መጥፋት የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው። ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን መጥፋቱ ባልተረጋገጠ ዕቃ ላይ ተገቢው የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈላል።

5/ በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ቆጠራ ከመካሄዱ ከ14 ቀን በፊት የታክሱ ባለሥልጣን ይህንኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት።

6/ ቆጠራ በሚካሄድበት ጊዜ በፋብሪካው ውስጥ የሚካሄድ ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ መቆም አለበት።

## ክፍል አምስት

## <u>የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬዕቃዎች</u>

28. <u>በተፈቀደለት አምራች የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ</u>

1/ የተፈቀደለት አምራች የመጨረሻውን ምርት ለማምረት የሚጠቀምባቸውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬዕቃዎች ራሱ የሚያመርት እና የኤክሳይዝ ታክሱ ስሌት በዋጋው በመቶኛ በሚሆንበት ጊዜ የጥሬዕቃው ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ትክክለኛው የገበያ ዋጋ ነው።

2/ ትክክለኛ ዋጋ ነው የሚባለው ጥሬዕቃውን ለማምረት የሚወጣው ወጪ እና ጥሬዕቃው ለሦስተኛ ወገን ቢሸጥ የሚታከለውን የትርፍ ህዳግ የሚያጠቃልል ይሆናል።

3/ የተፈቀደለት አምራች ጥሬዕቃውን ለሦስተኛ ወገን ጭምር የሚሸጥ ከሆነ፣ ለሦስተኛ ወገን የተሸጠበት ዋጋ የመጨረሻውን ምርት ለሚያመርተው ፋብሪካም ጥሬዕቃው የተሸጠበት ዋጋ እንደሆነ ይቆጠራል።

4/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወሰነው የእያንዳንዱ ጥሬዕቃ ዋጋ የተፈቀደለት አምራች በሚያቀርበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ መካተት አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## በቁርጥ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ዕቃዎች የመጠን አወሳሰን

29. በብዛት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው

1/ በመደበኛ ሁኔታ በብዛት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ታክሱ የሚሰላው በዕቃው ማሸጊያ ላይ የተመለከተውን ብዛት መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት በማሸጊያው ላይ ከተመለከተው በላይ ሆኖ ከተገኘ፣

ሀ) ዕቃው ውርስ እንዲደረግ፣

ለ) በተጨማሪው ዕቃ ላይ ወዲያውኑ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈል፣

ሐ) በአዋጁ አንቀጽ 39 መሠረት ቅጣት እንዲጣል፣

ሊወሰን ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ተጨማሪውን የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል ወይም ቅጣት እንዲጣልበት የሚደረገው አምራቹ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ይዞ የተገኘው ሰው እና አምራቹ በአንድነት እና በነጠላ ሊሆን ይችላል፡፡

## ክፍል ሰባት

## በአገር ውስጥ ጥሬዕቃዎች መጠቀምን ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ማስረጃ

30. የአገር ውስጥ ጥሬዕቃ ስለመጠቀም

1/ በአዋጁ በአገር ውስጥ ጥሬዕቃ ተጠቅመው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርቱ አነስተኛ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍሉ የተፈቀደ በሚሆንበት ጊዜ የተፈቀደለት አምራች ጥሬዕቃው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ እርሻ የተመረተ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

Ministry of Revenues
Documentation No 1

2/ ጥሬዕቃው በአገር ውስጥ የተመረተ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚቀርበው መረጃ የማስረከቢያ ሰነድ፣ ደረሰኝ፣ ከአምራቹ ጋር የተደረገ ውል እንዲሁም የአምራቹን ስም እና አድራሻ ይጨምራል፡፡

3/ የተፈቀደለት አምራች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩ ማስረጃዎችን ማቅረብ ካልቻለ ከውጭ አገር በሚመጣ ግብዓት ለሚመረቱ የተወሰነው የማስከፈያ መጣኔ ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ስምንት

## የምርት ብዛት ልኬት

31. <u>የተመረተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት ስለመመዝገብ - ጠቅላላ</u>

1/ የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚከናወነው በዋጋው በመቶኛ ወይም በቁርጥ ወይም በሁለቱም ቢሆንም የተመረተው ምርት ብዛት በትክክል ሊመዘገብ እና ሪፖርት ሊደረግ ይገባል፡፡

2/ በተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ወይም ለማከማቸት የሚውሉ መሣሪያዎች ወይም የማምረቻና የማከማቻ ቦታዎች የዕቃዎቹን ብዛት እና ዓይነት በትክክል ለማወቅ የሚያስችል የመቁጠሪያ መሣሪያ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡

3/ በእያንዳንዱ ፋብሪካ በምርት ሂደት ሊያጋጥም የሚችለው ተቀባይነት ያለው የብክነት መጠን በታክስ ባለሥልጣን ይወሰናል፡፡

32. <u>የፈሳሽ ዕቃዎች ብዛት ስለመለካት</u>

1/ የፈሳሽ ዕቃዎች ብዛት የሚለካው በሁለት ቁልፍ ደረጃዎች ይሆናል፣ እነዚህም፡-

ሀ) በምርት ሂደት ውስጥ ፈሳሹ በጥቅል ተከማችቶ በሚገኝበት ጊዜ፣

ለ) ፈሳሹ በሚታሸግበት ጊዜ፣

2/ ማናቸውም የተፈቀደለት አምራች በጥቅል ተከማችቶ የሚገኘው ፈሳሽ እና የታሸገው ፈሳሽ ብዛት እስከተቻለ ድረስ እኩል መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

3/ ፈሳሽ ምርቱን በማሸግ ሂደት የሚባክነው መጠን ተመዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

4/ የተፈቀደለት አምራች የማሸግ ተግባር ከመከናወኑ በፊት እና ከተከናወነ በኋላ ፈሳሹን የሚለካ አስፈላጊው ቆጣሪ ወይም ሌላ የመለኪያ መሣሪያ በፋብሪካው ውስጥ መግጠም እና የመሣሪያውን ንባብ በየጊዜው መወሰድ አለበት፡፡

5/ ማናቸውም የተፈቀደለት አምራች ፈሳሽ የሚለካውን ቆጣሪ ወይም ሌላ የመለኪያ መሣሪያ ትክክለኛነት በየጊዜው ማስመርመር እና የታክሱ ባለሥልጣን በሚጠይቅበት ጊዜ የምርመራው ውጤት እንዲሰጠው ማድረግ አለበት፡፡

6/ ፈሳሽ 10 ሊትር ወይም ከዚያ በታች በሆነ ቆርቆሮ፣ ጠርሙስ ወይም ሌላ አነስተኛ ማሸጊያ በሚታሸግበት ጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን የኤክሳይዝ ታክሱ በእያንዳንዱ ማሸጊያ ውስጥ ባለው ፈሳሽ ትክክለኛ መጠን ላይ ተመስርቶ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የተፈቀደለት አምራች የሚጠቀምበት ብዛትን የመቆጣጠሪያ ዘዴ "የአማካኝ ይዘት" ከሆነ የታሸገው ፈሳሽ አማካኝ ይዘት በቆርቆሮው ወይም በጠርሙሱ ወይም በህትመቱ ወይም በብረት በርሜል ወይም በእንጨት በርሜል የታሸገ በሚሆንበት ጊዜ በደረሰኙ ወይም በማስረከቢያው ሰነድ ላይ ከተመለከተው ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡

8/ የአማካኝ ይዘት ዘዴ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ በጥቅል የተያዘው ፈሳሽ ልኬት፣ ቀጥሎም የታሸገበት ዕቃ ብዛት፣ የማሸጊያው ልክ በትክክል መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ ይህም ልኬት ከ2% ያልበለጠ ብክነት ሊኖር እንደሚችል ከግምት ውስጥ በማስገባት የታሸገው ምርት በጥቅል ከተያዘው ፈሳሽ ጋር እኩል መሆኑን ማሳየት አለበት፡፡

9/ እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች በፈሳሽ ማከማቻው የተያዘው ፈሳሽ ብዛት ወደማሸጊያ ከተላለፈው ብዛት ያልበለጠ መሆኑን ለማረጋገጥ በማሸጊያዎች የመሙላቱ ሂደት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ አለበት፡፡

10. የተፈቀደለት አምራች የታክሱ ባለሥልጣን ለሚያከናውነው የክትትል ሥራ አጋዥ እንዲሆን በቁጥጥር ሥራው የተገኘውን ውጤት መመዝገብ እና ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተደጋጋሚ ከመጠን በላይ ፈሳሽን የመሙላት ተግባር መከናወኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያለ እንደሆነ የተፈቀደለት አምራች ተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## የአልኮል ጥንካሬን ስለመለካት

33. የአልኮል ጥንካሬ መለካት - በማብላላት የሚመረት

1/ የአልኮል መጠጦችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎች የሚያመርቱት ምርት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት የአልኮል ጥንካሬውን መሠረት በማድረግ ከሆነ የእያንዳንዱን ምርት የአልኮል ጥንካሬ መለካት አለባቸው፡፡

2/ የተፈቀደለት አምራች የሚገኘው ውጤት ከዚህ በታች በተመለከተው ዘዴ ተለክቶ ከሚገኘው ውጤት ጋር የሚጣጣም እስከሆነ ድረስ የአልኮል ጥንካሬውን ለመለካት ማናቸውንም ዘዴ ለመጠቀም ይችላል፡-

ሀ) ወካይ የሆነ ናሙናን በመውሰድ በተፈቀደው ዘዴ መሠረት ዝቃጭንና ጋዝን በማውጣት የተወሰነ መጠንን በ20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሙቀት ካልሲየም ሀይድሮክሳይድ ጨምሮ በማጣራት አልካሊን በማውጣት፣

ለ) የማጣራቱ ሥራ ከመከናወኑ በፊት የነበረው መጠን ሳይለወጥ በተጣራ ውሃ በ20 ዲግሪ ሲንቲግሬድ አልኮሉን በመለካት፣

ሐ) በተፈቀደ የፒክኖሜትር ልኬት መሠረት በአየር ውስጥ የሚኖረው ክብደት ከ20 ዲግሪ ሲንቲግሬድ መሆኑን ማረጋገጥ በሚቻል አኳኋን የተጣራው አልኮል ጥንካሬ የተለካ ከሆነ፣

መ) በፀደቀ የአልኮል ላቦራቶሪ ሠንጠረዥ መሠረት የምርቱ የአልኮል ጥንካሬ በተወሰነ መጠን አልኮል በመቶኛ ሲለካ በዚህ ዘዴ የአልኮሉ ክብደት በሠንጠረዥ ከሠፈሩ ሁለት አኃዞች መካከል ከሆነ የአልኮሉ ጥንካሬ በሊንየር ኢንተርፓሌሽን ይወሰናል፡፡

34. የአልኮል ጥንካሬ መለካት - ከፍተኛ የአልኮል መጠን ያላቸው

1/ የአልኮል መጠን መለካት ያለበት በአውቶማቲክ ዴንሲሜትር ነው፡፡ የሚከተሉት ሁለት መስፈርቶች ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

ሀ) ጥንካሬው መለካት ያለው "በባዶ በሚኖረው ክብደት" ሳይሆን "በአየር ውስጥ በሚኖረው ክብደት" ሲሆን በመጨረሻው "በአየር ውስጥ ወደሚኖረው ክብደት" መለወጥ ይኖርበታል፡፡

ለ) ልኬቱ በሚከናወንበት ጊዜ የፈሳሹ ሙቀት 20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ መሆን ያለበት ሲሆን፣ ልኬቱ በተለያየ ሙቀት መከናወን የሌለበት ሆኖ፣ በመጨረሻም ከ20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ጋር ተመጣጣኝ ወደሆነ ክብደት መቀየር ይኖርበታል፡፡

2/ አውቶማቲክ ዴንሲሜትርን በመጠቀም በትክክለኛ እና በእርግጠኝነት ክብደቱ መለካት አለበት፡፡

3/ ከአውቶማቲክ ዴንሲሜትር ውጪ የሆነ ሌላ የመለኪያ መሣሪያ ጥቅም ላይ የዋለ ከሆነ፣ ይህ ዘዴ በኤክሳይዝ ፈቃድ ላይ መመልከት ያለበት ሲሆን፣ ትክክለኛነቱ በተወሰነ ጊዜ ልዩነት መረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል አሥር

## የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከተፈቀደለት ፋብሪካ ስለማውጣት

35. ሽያጭ ከተከናወነ በኋላ ዕቃዎችን ከፋብሪካ ስለማውጣት

1/ የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችን ከፋብሪካው እንዲወጣ በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል፡፡

2/ በታወቀ ሽያጭ ከተፈቀደለት ፋብሪካ የወጡ ዕቃዎች የታክስ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የማስረከቢያ ሰነድ እና የሽያጭ ደረሰኝ ሊቆረጥባቸው ይገባል፡፡

3/ ወደፊት ሽያጫቸው የሚከናወን ዕቃዎች ካልሆኑ በስተቀር ከፋብሪካ በሽያጭ በሚወጡ ዕቃዎች ላይ ከፋብሪካው ከመውጣታቸው በፊት የሽያጭ ደረሰኝ መቆረጥ አለበት፡፡

4/ ከተፈቀደለት ፋብሪካ ከወጡ በኋላ የሚሸጡ ዕቃዎች ከፋብሪካው ከወጡበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለደንበኛው ተሸጠው የሽያጭ ደረሰኝ ሊቆረጥላቸው እና ሽያጩ ከማስረከቢያው ሰነድ ጋር እንዲጣጣም መደረግ ይኖርበታል፡፡

36. ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካ ስለሚወጡ ዕቃዎች

1/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ሽያጭ የሚከናወነው ከፋብሪካው ውጪ በሚሆንበት ጊዜ ለሽያጭ እንዲውሉ ከፋብሪካው በሚወጡበት ጊዜ የምርቱን ልዩ መጠሪያ፣ ዓይነት እና ብዛት የሚገልፅ የማስረከቢያ ሰነድ መዘጋጀት አለበት፡፡



of Revenues
Documentation No 1

2/ የማስረከቢያው ሰነድ በታክሱ ባለሥልጣን በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝር መረጃዎችን ሊይዝ ይገባል፡፡

3/ ሽያጭ በሚከናወንበት ጊዜ የተሸጠውን ዕቃ ብዛት፣ ዓይነት፣ ልዩ መጠሪያ፣ ለታክሱ ባለሥልጣን አስቀድሞ የተገለፀውን ለኤክሳይዝ ታክስ መሠረት የሆነውን ዋጋ፣ የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ልክ እንዲሁም የገዥውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና አድራሻ የሚያሳይ ደረሰኝ ተዘጋጅቶ ለእያንዳንዱ ገዥ መሰጠት አለበት፡፡

4/ የሽያጩ ደረሰኝ ዕቃው ከፋብሪካ በወጣበት ጊዜ የተመዘገበውን የማስረከቢያውን ሰነድ ቁጥር መያዝ ይኖርበታል፡፡

5/ የሽያጭ ደረሰኙ ቅጂዎች ሊኖሩት የሚገባ ሲሆን፣ ዋንኛው ለደንበኛው ይሰጣል፣ ቀሪው ከማስረከቢያው ሰነድ ጋር ይያያዛል፡፡

6/ ከፋብሪካ የወጣውን፣ የተሸጠውን እና ተመላሽ የተደረገውን ዕቃ በትክክል ለማስታረቅ እንዲቻል በሽያጭ ደረሰኙ ላይ የማስረከቢያው ሰነድ ቁጥር እንዲሁም በማስረከቢያው ሰነድ ላይ የሽያጭ ደረሰኙ ቁጥር መፃፍ አለበት፡፡

## ክፍል አሥራ አንድ

## ጌጣጌጥ፣ ጨውና የፕላስቲክ መያዣ

37. በጌጣጌጥ ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ

1/ የከበሩ ማዕድናትን (አልማዝ፣ ወርቅ፣ ብር እና/ወይም ኦፓል ወ.ዘ.ተ) በክፊል የያዙ ጌጣጌጦች የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በጌጣጌጥነት ያልተሠራ ጥሬ የከበረ ማዕድን (አልማዝ፣ ወርቅ፣ ብር፣ ኦፓል ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑት) የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልበትም፡፡

3/ በጌጣጌጥ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ ጌጣጌጡ እንደተመረተ ይቋቋማል፡፡

4/ ለጌጣጌጥ አምራቾች ጥሬው የከበረ ማዕድን እንደጥሬዕቃ ይቆጠራል፡፡

5/ የከበሩ ማዕድናትን (አልማዝ፣ ወርቅ፣ ብር፣ ኦፓል ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ) የሚያመርቱ የማዕድን ኩባንያዎች ለኤክሳይዝ ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የለባቸውም፡፡



Ministry of Revenues ... Documentation No 1

6/ ጌጣጌጥ የሚያመርቱ ድርጅቶች ያመረቱትን ጌጣጌጥ የሸጡበትን የማስረከቢያ እና የሽያጭ ሰነድ መያዝ አለባቸው፡፡

7/ የጌጣጌጥ አምራቾች በተፈቀደለት አምራችነት የመመዝገብ እና ሰነዶችን የመያዝ ግዴታ አለባቸው፡፡

## 38. <u>በጨው ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ</u>

1/ ጨው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት በመሆኑ ጨው ወደአገር የሚያስገባ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያመርት ሰው ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

2/ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት እና ለተለየ ዓላማ እንዲውል ለማድረግ በፋብሪካ የሚመረት ጨው በድጋሚ የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልበትም፡፡

## 39. <u>በፕላስቲክ መያዣ ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ</u>

1/ የፕላስቲክ መያዣ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት በማምረቻው ቦታ ሲሆን፣ በአዋጁ በተደነገገው መሠረት በኪሎግራም የተወሰነውን የማስከፈያ መጣኔ ተፈፃሚ በማድረግ ይሆናል፡፡

2/ በማምረቻ ቦታው የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት የፕላስቲክ መያዣ በዕቃ መያዣነት ከዕቃ ጋር ወይም ለብቻው በሚሸጥበት ጊዜ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ አይኖርም፡፡

3/ ለአዋጁና ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም "የፕላስቲክ መያዣ" ማለት በዕቃ ማጓጓዣነት የሚያገለግል የፕላስቲክ ዘንቢል ሲሆን፣ የዕቃ ማሸጊያን አይጨምርም፡፡

## 40. <u>ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር የተያያዘ ሠንጠረዥ</u>

የጉምሩክ ታሪፍ አመዳደብና ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር የተያያዘው ሠንጠረዥ ተጣጥመው ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ የሚያስችል ማብራሪያ በገንዘብ ሚኒስቴር ሊወጣ ይችላል፡፡

41. <u>መመሪያው የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 06 ቀን 2013 ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ 05 ቀን 2013 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*